# የታሪክ ጎማ እየከነፈ ነው!!

ታሪኩ አባዳማ - ጥቅምት 2004

ሾፌር አልባው የዘመናችን የታሪክ ጎማ በፍጥነት እየከነፈ … በጨካኝ ገገርዎች አንገት ላይ በጭካኔ እየተሽከረከረ ነው። አምባገነኖች በከፋፍለህ ግዛ ወይንም ስለላ መረብ እና ጠመንጃ ሀይል አገዛዛቸውን ማቆየት እንደተሳናቸው ደግሞ እንደገና እያረጋገጠ ነው። ያለ መሪ ፓርቲ እና ቀስቃሽ ካድሬ ከቱኒዚያ የተቀሰቀሰው የታሪክ ጎማ አረቡን አለም አዳርሶ በሊቢያ አቋርጦ በመክነፍ ላይ ሲሆን አምባገነን ገገርዎች በተገኙበት አድራሻ ሁሉ ታድነው የሚወገዱበት ህዝባዊ ቁጣ እየተቀጣጠለ መፋጀቱን ቀጥሏል።

ከትናንት እስከ ዛሬ - ከቻውቼስኩ እስከ ጋዳፊ ፤ ከሂትለር እስከ ኢዲ አሚን ፤ ከስታሊን እስከ መለስ ዜናዊ እና ኢሰይያስ አፈወርቂ ብሎም ሮበርት ሙጋቤ - አምባገነን ገገርዎች ሁልግዜም በራሳቸው አይምሮ ውስጥ በፈጠሩት ምናባዊ አለም እንደሚኖሩ ይታወቃል። በኢኮኖሚ እና ቴክኖሎጂ በላቀ እንደ ጀርመን ባለ አገር ይሁን ወይም በረሀብተኛነት የታወቀ እና በዕድገት ደረጃ እጅግ በደቀቀ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አገር ውስጥ አምባገነኖች መሰረታዊ ተፈጥሯቸው ከነባራዊ እውነት ጋር የተፋታ ፣ ስለ ዓለም ቀርቶ ስለሚቆጣጠሩት አገር ያላቸው ግንዛቤ የተምታታ ውል የሌለው ቅዠት መሆኑም በተጨባጭ እያየን ነው።

ማን ይደፍረናል ፣ ማንስ አጠገባችን ይደርሳል ብለው ስለራሳቸው ዘላለማዊነት የሰበኩ ጥቂት የማይባሉ ገገርዎች እንደ ሸክላ ተሰባብረው ሲንኮታኮቱ በዚች አጭር ዘመናችን በተደጋጋሚ ለማየት በቃን። ቤተ-መንግስታቸውን በወርቅ አልማዝ አንቆጥቁጠው አሚሚታቸው ግን በአይጥ ጉርጓድ የሆነውን ፤ በስለላ እና ልዩ ጥበቃ ብርጌድ ተከበው የህዝብ ቁጣ ሲገነፍል ግን ድመት እንዳየች አይጥ ሲፈተለኩ ዘመናቸው በውርደት ያከተመውን አስተዋልን። በአገዛዝ ዘመናቸው ህግ እና ተጠያቂነትን ረግጠው እንደኖሩ ሁሉ በተራቸው በህግ ጥመኛ ህዝብ ክንድ ተገፍትረው ደማቸው ሲፈስ ለመታዘብ ችለናል - ዋ ጋዳፊ!!

በዚህ አጭር የዕድሜ ዘመናችን እንኳ በወዛደሩ ፈላጭ ቆራጭ (Dictatorship of the proletarian) ስም ስልጣናቸውን አደላድለው ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል ምስራቅ አውሮፓን የሁዋልዮሽ ሲጎትቱ የቆዩት ኮሚኒስቶች - የኛንም ኮሎኔል ጨምሮ - አይወድቁ አወዳደቅ ተገርስሰው ወደ ታሪክ ትቢያ ሲወረወሩ አይተናል - ። ዛሬ ደግሞ የአረቡን ዓለም ቀፍድደው በመያዝ ገደብ የለሽ ስልጣንና ሀብት ሲያማስኑ የነበሩ ገገርዎች በህዝብ ላይ ላደረሱት ግፍ እና በደል ሂሳብ በማወራረድ ላይ ይገኛሉ። በንፁሀን ዜጎች ደም እጃቸው የከረፋ ገገርዎች ፣ በንቅዘት እና ዘረፋ ሀብት የደለቡ አምባገነኖች በህዝብ ቁጣ እየተፈረካከሱ ነው። የአምባገነኖች ጠረን እየከሰመ ነው።

የግብፁ ሙባረክ ዙፋን ላይ ለመቆየት ገና ብዙ ዘመን ይቀረኛል - ስልጣኔን የምለቀው 'የምርጫ ዘመኔ ሲያበቃ ከአራት አመታት በሁዋላ ነው' ብለው ለይስሙላ ስላካሄዱት ምርጫ ህጋዊነት ቲቪ መስኮት ላይ ቆመው ቢመፃደቁም — ወታደር አዝምተው በሁለት ሳምንት ብቻ የስምንት መቶ ግብፃውያን ደም ቢያፈሱም ሀያሉን የታሪክ ጎማ ከመሽከርከር ሊገቱት አልቻሉም። ከስልጣን ተገፍትረው ወረዱ ፤ ፀጉራቸውን ቀለም ቀባብተው በስልጣን ለመቆየት አራት ዓመት ይቀረኛል ያሉት ሙባረክ በፍርድ ቀን አደባባይ ለመቆም ግን 'ጉልበቴ አይችልም… አርጅቻለሁ' አሉ። ለመግዛት ብቁ ነኝ ብለው ያስነገሩት አዋጅ ሳይዘነጋ 'ደካማ ነኝ ፣ በሽተኛ ነኝ…' ዕድሜዬ ፍርድ ቤት ለመቆም አያበቃኝም ሲሉ ያፌዙት ሙባረክ የአካል ብቻ ሳይሆን የሞራል ብቃታቸውን በሚመለከት ህዝቡ አስቀድሞ የነገራቸው እውን መሆኑን ግን እራሳቸው መሰከሩ - ይሁንና በወሳንሳ ተገፍተው ፍርድ ቤት ከመቅረብ ሌላ አማራጭ አላገኙም። ህግ አይኑን ሲያፈጥ አምባገነን ጉልበቱ ይሚሽሻል - ወሳንሳ አቅርቡልኝ ይላል።

ኮሎኔል ገዳፊ ደግሞ BBC ጋዜጠኛ ፊት ሲቀርቡ 'ዲሞክረሲ እና ዕድገት ያጎናፀፍኩት ህዝቤ ይወደኛል ይሞትልኛል…' ብለው በለሰለሰ አንደበት ተናገሩና ዞር ብለው ደግሞ ምሽቱን በሚሰራጭ በራሳቸው ራዲዮና ቲቪ ያንኑ ህዝብ 'አንተ አይጥ ሁላ ከየጎዳናው ለቅሜ ጉርጓድ ባልከትህ እኔ አይደለሁም' ብለው አረንጓዴውን መጣፍ በማጣቀስ በቁጣ ሲወዛወዙ አገኘናቸው። መለስ ዜናዊ ምዕራብ ፊት ስለዲሞክረሲ መንሰራፋት ሲዘባርቁ ውሎ እራሱ ፓርላማ ሲደርስ ደግሞ 'ተቀዋሚ ነኝ' የሚሉ አሸባሪዎችን አድነን ጉርጓድ እንከታለን እንደሚለው አይነት መሆኑ ነው። የአምባገነኖች ተፈጥሮ አንድ ነው - መለስ እና ጋዳፊ ካንድ ባህር የተቀዱ የሁለት አገር አምባገነኖች ናቸው።

ጋዳፊ ሮጠው… ተደብቀው… ብቅ ጥልቅ ብለው… 11ኛው ሰዓት ላይ የተገኙት እሳቸውም እኛም በላልጠረጠርነው የውሀ መውረጃ ቱቦ ውስጥ ነበር። 'ዲሞክረሲ' ያጎናፀፉት እና 'የሚወዳቸው…' ህዝብ እንደ ሰው ሳይሆን እንደ አደገኛ አውሬ ጨፍጭፎ ገድሏቸዋል። እሳቸው አርባ ዓመት ሙሉ እንደ መሪ ለሊቢያ ህዝብ ያስተማሩት ስለ ሰብአዊ ክብር ወይም የህግ የበላይነትን ሳይሆን ጭካኔ እና ህግ አልባነትን ነበር - ህዝቡም ከሳቸው በቀሰመው በዚያው በሰለጠነበት መንገድ የመጨረሻውን ፍርድ አበረከተላቸው።

ብዙ ታዛቢዎች የጋዳፊ አገዳደል 'ኢሰብአዊ…' ነበር ብለው ሲተቹ ሰምተናል - ለመሆኑ ይህ ህዝብ ሰብአዊነቱን ከየት ያምጣው? ብሎ መጠየቅ ግን ብልህነት ይመስለኛል። በጋዳፊ አገዛዝ በሉት አመራር ዘመን ከጎሳ መድልዎ እና ከግለሰብ አምልኮ የፀዳ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ አሰራር እንዲፈጠር የተደረገ ሙከራ ነበር? በሳቸው አመራር በስግብግብነት እና ለከት ባጣ ራስ ወዳድነት መንፈስ የአገሪቱን ሀብት በቤተዘመድ እና ዘር ቆጠራ ተደራጅቶ ፣ በይሉኝታ ቢስነት ብሎም 'ምን ታመጣላችሁ' በሚል እብሪት አገሪቱን ከመዝረፍ ውጭ ለህዝቡ ያቆዩት ምን አለ? ተጠያቂነት እና ግልፅነት በህግ የበላይነት ላይ እንዲሰርፅ የማድረግ መንግስታዊ ድርሻቸውን ተወጥተዋል? ብሎ ጉዳዩን በጥልቀት መመርመር መልካም ነው። ነገ እኛም አገር የሚሆነው ይኸው ነውና!!

ጋዳፊ በተያዙበት ሁኔታ (አፍላ የጦር ፍልሚያ) እና ቦታ (የውሀ ቱቦ) እንዲሁም ግዜ (ስልጣን ሹም ሽር) ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወስደው ፣ የዋስ መብታቸው ተከብሮ እና የክስ ቻርጅ ደርሷቸው ዳኝነት እንዲያገኙ ተጠብቆ ከሆነ ግምቱ 'ተምኔታዊ ሰብአዊነት' ነው። እሳቸው አርባ ዓመት በገዟት አገር ለዚህ አይነቱ የሰለጠነ እና ሰብአዊ አያያዝ ያዘጋጁት ተቋም ወይም ህዝብ የለም። ህዝብ የመብት ጥያቄ አንግቦ በተነሳበት ሰዓት አልጋ ወራሽ ልጃቸው ቲቪ መስኮት ላይ ተከፍሶ 'እርፉችሁ ካልተቀመጣችሁ… ሊቢያን የደም ባህር እንዳርጋታለን' ነበር ያለው። አርባ ዓመት ተሸክሞ የሰገደላቸውን ህዝብ ውለታ ለመክፈል የቀራቸው ደም 'እንደ ጅረት' ማፍሰስ ብቻ ነበር - እርግጥም የቻሉትን ያህል ደም አፈሰሱ። ጋዳፊን ከዙፋን ለማውረድ ከሀምሳ ሺህ በላይ ሊቢያውያን ማለቅ ግድ ሆኖባቸዋል።

ሩማንያን ሀያ ሰባት አመታት ሙሉ በስለላ እና አፈና ተቋም ፀጥ አድርገው የገዙት ቻውቼስኮ ከጋዳፊ ባልተሻለ መንገድ በቃ ብሎ በተነሳ ህዝብ ፍርድ በጥይት ተደብድበው ነበር የተገደሉት - በወቅቱ የቻውቼስኮ ሚስት ኤሌና ከባላቸው ጎን ቆመው መረሸናቸው የሚዘጋ አይደለም (Elena እንደ ዛሬዋ አዜብ ጎላ የእርጎ ዝምብ የነበሩ ሴት መሆናቸው ይነገራል)። ወ/ሮ ኤሌና ወደሚረሸኑበት ማማ ሲነዱ የሚገፈትራቸውን ወታደር 'I was like a mother to you' 'እንደ እናታችሁ አልነበርኩምን?' በማለት ምህረት እንዲያደርግላቸው ልብ የሚያራራ ቃል ጣል አድርገው እንደነበር በወቅቱ በሰፊው ተዘግቧል። እውን ኤሌና ቻውቼስኮ ሰብአዊ መብቱ ለተረገጠው እና በስራ እጦት የህይወት ዋስትና ለተነፈገው የሩማንያ ህዝብ እንደ እናት ነበሩ? እውን የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ ጎላ ለኢትዮጵያ ህዝብ እንደ እናት ናቸው? እሳቸው እናት ከሆኑ አባት ማን ሊሆን ይሆን? ሁሌ ሳስበው የሚገርመኝ አባባል ነው።

መለስ ዜናዊ - ወያኔ አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ማግስት ለመላው ዓለም እንዳወጀው - 'ከንግዲህ ወዲህ ማንም ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ ዕምነቱ አንዳችም ችግር እንደማይገጥመው ፣ የመፃፍ እና የመደራጀት ብሎም የመቃወም መብት 'ሳይሸራረፍ' የተጋገጠባት አገር መሆኗን አወጀ። እውነቱ ግን ሀያ አመታት ሳያቋርጥ ለዚህ ፖለቲካ ድርጅት ሰራሁ ፣ ጋዜጣ ላይ ፃፍክ እየተባለ በወያኔ እጅ መገደሉ ፣ መታገቱ ፣ ማዋከቡ እና እንደ አውሬ መታደኑ ያላባራ መሆኑን ነው።

የታሪክ ጎማ አቧራ እያጨሰ ይከንፋል - ድምፁ ሲያሰገመግም ተኝተው የሚያዳምጡ ፣ እንዲያውም አልሰማንም አላየንም የሚሉ አሁንም አጠገባችን አሉ። የታሪክ ጎማ ግን ሀያል ነው! እውቅና አይጠይቅም - ከተፍ… ሽው እልም ነው። ጎሳ ከለላ ለማድረግ ሲርት Sirte ወደተባለች ትውልድ መንደራቸው ያፈገፈጉት ጋዳፊ ከጎማው ጥርስ ማምለጥ አልሆነላቸውም - ክፉ ቀን ሲመጣ ያስጠልለኛል ብለው በከፋፍለህ ግዛ ያዘጋጁት መንደር እንኳ ከውሀ ቱቦ ሌላ ሊያቀርብላቸው የቻለው ነገር የለም - አልታደጋቸውም።

አፋኝ መንግስታት የተንሰራፉበትን ምድር እያሸተተ አቅጣጫውን በማስተካከል የሚከንፈው የታሪክ ጎማ በአረቡ ዓለም የጀመረውን የጭፍለቃ ገድል በስኬት በማገባደድ ላይ ቢሆንም መሽከርከሩን ግን አላቆመም - የአምባገነን ክርፋት መትንፈሻ ወዳሳጣት ጥቁር አፍሪካ ምድር አፍንጫውን ቀስሯል - ጋዳፊን አያርገኝ!!